ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ታህሣሥ 18 ቀን 2001 ዓ.ም.

- የወያኔ ባለስልጣናት ነጋዴዎችን በማስገደድ በይፋ ገንዘብ አምጡ ማለት ጀመሩ፣

- አራት ታዋቂ ነጋዴዎች እራሳቸዉን ገድለዉ ተገኙ፣

- የመለስ ባለቤት አዜብ መስፍን ከተስፋዬ መርሳ ጋር በድብቅ የዉጭ ገንዘብ ስትመነዝር እንደነበረ ተጋለጠ፣

- ከ12 ዓመት እስራት በኋላ የተፈታዉ ታምራት ላይኔ ሰበካ ጀመረ፣

- ህላዊ ዮሴፍ ከተባረረ አንድ ዓመት በኋላ ወደ ስራ ተመለሰ፣

- የወያኔ ቴሌቪዢንና ራዲዮ በመለስና በበረከት ቁጥጥር ስር እንዲሆን ተደረገ፣

የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል ።

ዝርዝሩን ከሚቀጥለዉ ገፅ ጀምረዉ ያንብቡ <<<<>>>>

የወያኔ ስርዓት ቀንደኛ አቀንቃኝ እና ተሳታፊ የነበረው የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ተስፋዬ መረሳ በአዲስ አበባ ነጋዴዎች ላይ ሲሰራ የነበረው ሸፍጥ መጋለጡን በደል የደረሰባቸው የንግዱ ማህበረሰብ አጋለጡ::

የህወሀት አባሉ ተስፋዬ መረሳ የነበረውን ስልጣን መከታ በማድረግ የንግዱን ማህበረሰብ አባላት በተለይም ታዋቂ የመርካቶ ነጋዴዎችን ሰበብ አስባብ እየፈለገ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ እያስፈራራ ገንዘብ ሲቀበል ነበር ያሉት የችግሩ ሰለባ ነጋዴዎች አሁንም በርካታ ባለስልጣናት በቀጥታ ገንዘብ አምጡ እያሉ ነጋዴዎችን በስልክ እያስፈራሩ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

የወያኔ ስርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከህዝብ እየተጠላና እየተተፋ በሄደበት ወቅትና እርስ በርስ ባለስልጣናቱ ሽኩቻቸው እያየለ በመጣበት በዚህ ወቅት ያለ አንዳች ይሉኝታ ነጋዴውን በግዴታ ገንዘብ አምጣ እያሉ ማስፈራራት መጀመራቸው የስርዓቱ መዳከምና የመጨረሻው መጀመሪያ መሆኑን ያሳያል ሲል ዘገባው ገልፆዋል::

ወትሮም ቢሆን ለግል ጥቅማቸው የቆሙት የወያኔ ባለስልጣናት ከዚህ ቀደም በእጅ አዙር ሲያደርጉት የነበረውን ዝርፊያ አሁን በቀጥታ ከነጋዴዎች ላይ በግዴታ « ገንዘብ አምጡ » ማለት መጀመራቸውንም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በተለይ በደብረዘይት ከተማ አቅራቢያ በተከፈተው የቁማር ቤት ውስጥ በብዙ ሺህ ብር ቁማር መጫወት የጀመሩት እነዚሁ የወያኔ ባለስልጣናት በቀን በመቶ ሺህዎች ብር ድረስ ከህዝብ ካዝና እያወጡ መርጨት ስለለመዱ ይህም አልበቃ ስላላቸው ብቻ ነጋዴዎቹን እያስፈራሩ በግዴታ ገንዘብ መቀበል መጀመራቸውን ዘገባው ገልፆዋል::

በቅርቡ አራት ታዋቂ ነጋዴዎች የራሳቸው የተለያዩ ምክንያቶች እያስጨነቁዋቸው የነበረ ቢሆንም ይበልጥ ግን የወያኔ ባለስልጣናት ባደረሱባቸው ወከባና ማስፈራራት እራሳቸውን ለማጥፋት እንደተገደዱ የገለፀው የደረሰን ዘገባ ውስጥ ውስጡንም በርካታ ነጋዴዎች ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቀው እንደሚገኙ አጋልጦዋል::

የጥሬ እቃ መግዣ የውጭ ምንዛሪ አጥተው ስራቸውን ለማቆም በተገደዱበት በዚህ ወቅት ላይ በእሳት ላይ ቤንዚን እንዲሉ ነጋዴዎቹን በግዴታ እያስፈራሩ ገንዘብ አምጡ ማለታቸውና ያንን ገንዘብ መክፈል ካልቻሉ የሚደርስባቸው ችግር ከፍተኛ መሆኑን በማስፈራራት እየነገሩዋቸው በንዴት እራሳቸውን ማጥፋት እንደጀመሩ ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ብቻ የይርጋ ኃይሌ ህንጻ ባለቤት ልጅ የሆነው አቶ ምክንያቱ ኃይሌ የተባለው የአሴ ሴራሚክስ እና የአሴ ማርብል ባለቤት ሐሙስ ታህሳስ 9 ቀን 2001 ዓ. ም በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እራሱን ገድሎ የተገኘ መሆኑን የገለፀው ዘገባ

ከሁለት ቀን በሁዋላ ደግሞ የጌታነህ ትሬዲንግ ፤የተዘጋጁ ልብሶችን፤ ብትን ጨርቆችን፤ ድርና ማግ አስመጪና አከፋፋይ ድርጅት ባለቤት የሆነው አቶ ዮሐንስ ጌታነህም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ እራሱን አጥፍቶ መገኘቱን ዘገባው አስረድቶዋል::

በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ አራት ታላላቅ ሀብታሞች በተለያዩ ምክንያቶች እየሞቱ መሆኑ እየተገለፀ ባለበት ወቅት ዐርብ እለት ደግሞ የኮንኮርድ ሆቴል ባለቤት መኪናቸውን እያሽከረከሩ በሚጉዋዙበት ወቅት ከግንብ ጋር ተጋጭተው ወደ ድልድይ ውስጥ ገብተው መሞታቸውን የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ወያኔ ሁሉን ለራሴ እያለ ለፍተውና ጥረው ግረው የሚኖሩትን ባለ ሀብቶች የተለያዩ ጫናዎችን እያሳረፈባቸው እንዳይሰሩ ከፍተኛ እንቅፋት እየሆነባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ስራ በሌለበት ፤ ግብር ምን እንከፍላለን እያሉ በተጨነቁበት በዚህ ወቅት ከፖለቲካ ጋር እያያዙባቸው በማስጨነቃቸው እራሳቸውን ለማጥፋት እየተገደዱ መሆኑን ዘገባዎች እየገለፁ ሲሆን የኮንኮርድ ሆቴል ባለቤትም ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ እራሳቸውን ከነመኪናቸው ድልድይ ውስጥ ከትተው መገኘታቸው ታውቆዋል ሲል የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት አንድም የውጭ ምንዛሪ በሀገሪቱ ባንኮች ውስጥ የሌለ በመሆኑ ነጋዴዎቹ ስራ ለማቆም እንደተገደዱ የገለፀው ዘገባ አንዳንድ ፋብሪካዎችም ከውጭ የሚገቡ የጥሬ እቃ ለመግዛት የውጭ ምንዛሪ የለም ስለተባሉ ፋብሪካዎቹ ስራ ከማቆማቸውም በላይ ሰራተኞቹን ለመበተን እንደተገደዱ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል:: በሀገሪቱ ውስጥ አሉ ከተባሉት ሀብታሞች መካከል የሚመደቡት እነዚሁ ሙዋች ነጋዴዎች ለጉዋደኞቻቸውና ለቅርብ ሰዎቻቸው ገንዘብ አበድረው ተካክደው ነው እራሳቸውን ያጠፉት እየተባለ እንዲናፈስ ተደረገ እንጂ ዋናው ግን የወያኔ ባለስልጣናት በነጋዴዎቹ ላይ የሚያደርሱት ገደብ አልባ በደል እና ግፍ ነው ያለው ዘገባው በዚህ ከቀጠለ ሌሎችም በርካታ ነጋዴዎች ተመሳሳይ እርምጃ ከመውሰዳቸውም በተጨማሪ በርካቶች ሀገሪቱን ጥለው ሊሰደዱ እንደሚችሉ በንግዱ ማህበረሰብ በኩል ከወዲሁ ስጋት እያሳደረ መገኘቱንም ዘገባው አብራርቶዋል::

በተለይ በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ባለስልጣናት በስርዓቱ ላይ ተስፋ ስለቆረጡ ነጋዴዎቹ ከፍተኛ ገንዘብ እንዲሰጡዋቸው ከማስገደዳቸውም በተጨማሪ በፖለቲካ አሰብበው የግፎች ሁሉ ግፍ እንደሚፈጸምባቸው ማስፈራሪያ ስለሚደርስባቸው በንዴትና በብስጭት ቅፅበታዊ እርምጃ እየወሰዱ እራሳቸውን፤ ቤተሰቦቻቸውንና ሀገራቸውን ሊጎዱ እንደሚችሉ እና ይህንን ሁኔታ ቆም ብለው አስበው በረጋና በተረጋጋ ሁኔታ መወሰን እንዳለባቸውና ስሜታዊ መሆን እንደሌለባቸው የእድሜ ባለፀጋ አባቶች ምክር መለገሳቸውን ዘገባው አብራርቶዋል::

ወያኔ ስልጣን ከተቆጣጠረ ጊዜ ጀምሮ በነጋዴው ማህበረሰብ ላይ የተለያዩ በደልና ግፎችን ሲፈፅም የቆየና አሁንም እየፈጸመ ያለ መሆኑን የገለፀው ዘገባው ኤፈርት ብሎ ባቋዋቋዋመው ግዙፍ ድርጅት አማካኝነት የንግድ እንቅስቃሴውን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ ነጋዴውን ከእንቅስቃሴ ውጭ ለማድረግ ሲሰራ የቆየና አሁንም እየሰራ ያለ መሆኑንም ጨምሮ አስረድቶዋል::

ከኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ተዘርፎ በታጋዮች ስም የተቋዋቋዋመው በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ትልቁ እንደሆነ  የሚነገርለት ይኸው ኤፈርት የተሰኘው ግዙፍ የወያኔ ድርጅት በአሁኑ ሰዓት የጥቂት የወያኔ ባለስልጣናት ንብረት ሆኖ አመታዊ ትርፍ ድርሻቸውን የተከፋፈሉ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ወያኔ  በሁሉም የንግድ ዘርፎች ተሰማርቶ ነጋዴውን ለማሽመድመድ እየተራወጠ መሆኑ ሳያንሰው እንደገና በግል ደረጃ በስም እየጠሩ ያልለፉበትን ገንዘብ አምጡ እያሉ ማስፈራራት መጀመራቸው አሳፋሪ ነው ሲልም ገልጾዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን  የሀገሪቱን ሀብት ዘርፋ አንቱ ከተባሉ ሀብታሞች በላይ ሀብት ያከማቸች ከመሆኑዋም በላይ በዘመዶቿዋ ስም የተለያዩ ኮንስትራክሽን ድርጅቶችን አቋዋቁማ እየተንቀሳቀሰች መሆኑዋን በአሁን ሰዓት የሰንሻይን  ኮንስትራክሽን እና የአልፋ ዩኒቨርስቲ አክስዮን ድርሻ እንዳላትና በሌሎችም የንግድና የስራ መስኮች ተሰማርታ ያለች መሆኑን  ታውቃል::

በተለይ በውጭ ምንዛሪ እጦት የሀገሪቱ ነጋዴዎች ዕቃ ከውጭ ሀገር ገዝተው ማስገባት በተቸገሩበት ወቅት አዜብ መስፍን ከአክስትዋ  ልጅ ባል  ከሆነው ተስፋዬ መረሳ ጋር በመሆን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በምስጢር የውጭ  ምንዛሪ  በጥቁር ገበያ ህገ ወጥ ከሆኑ ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር የውጭ ሀገር ገንዘቦችን እየመነዘረች እንደ ልብዋ  እየተንቀሳቀሰች መሆኑም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

በፀረ ሙስና ተብዬ የወያኔ ማስመሰያ መስሪያ ቤት ውስጥ ከ5 ፋይሎች በላይ ተከፍተውበት የነበረው ተስፋዬ መረሳ ከዚህ ቀደም ወደ አሜሪካ ጠፍቶ ኮብልሎ የነበረ ቢሆንም በወያኔ ውስጥ የነበረው የፖለቲካ  ትኩሳት ግሎ የነበረበት ወቅት በመሆኑ በባለቤቱ ዘመድ አዜብ መስፍን አማላጅነት ተመልሶ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ተደርጎ አልጠፋሁም ለማሰኘት ተደጋጋሚ መግለጫ ሲሰጥ የከረመ እንደነበር ያስታወሰው ዘገባ ጊዜውን ጠብቆ በመለስ ሚስት አማላጅነት እንደመጣው ሁሉ ተመልሶ  በእሱዋ በኩል ዲቪን ሰበብ አድርጎ ጉዋዙን ጠቅልሎ አሜሪካ አትላንታ ሊገባ እንደቻለ ዘገባው አብራርቶዋል::

የቀድሞው የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ ከ12 ዓመት እስራት በሁዋላ ከእስር ቤት ሲወጣ የቀድሞ ፖለቲከኛነቱን ቀይሮ የክርስትና እምነት ተከታይ ሆኖ ለምዕመናን ሰበካ መጀመሩ ታወቀ::

ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ. ም. ከቃሊቲ እስር ቤት የተፈታው ታምራት ላይኔ ከእስር ቤት በወጣ በሁለተኛ ቀን ታህሳስ 12 ቀን 2001 ዓ. ም. በቦሌ የወያኔ ንብረት በሆነው ሜጋ ህንፃ አካባቢ በሚገኘው « ተቀባ »በተሰኘው የፕሮቲስታንት እምነት ተከታዮች ቤተክርስቲያን በመገኘት ሲያለቅስና ሲያስተምር የነበረ መሆኑን ዝግጅቱን የተከታተሉ ወገኖች ገልፀው ታምራት በሚሰብክበት ወቅት « ዳኝነት የሚሰጠው ፤ ፍትህ የሚሰጠው እየሱስ ብቻ ነው »እያለ ስለ ራሱ ይናገር እንደነበረ አስረድተዋል።

ከዚህ በሁዋላ በየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ አልቀላቀልም ያለው ታምራት ላይኔ ከ12 ዓመት እስራት በሁዋላ አማኝ ሆኛለሁ ቢልም ስልጣን ላይ በነበረ ጊዜ በአርባ ጉጉ ፤ በጅጅጋ እና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች በመገኘት « ነፍጠኛውን በሉት » እያለ ህዝብን ከህዝብ ሲያጨፋጭፍ እና እንዲተላለቅ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን፤እርስ በርስ ውስጣቸው በተነሳ ሽኩቻ ገንዘብ ዘርፎዋል ተብሎ ይህንንም አምኖ ለእስር የተዳረገ ቢሆንም ገና ያላወራረደው የህዝብ እንባ እና ደም መኖሩንና በተለይ በዚህ ዓይነት መንገድ የሰራውን ግፍ እና የፈፀመው ወንጀል ለመሸፈን ሆን ብሎ የገባበት ነው ሲሉ በጥርጣሬ የሚገልፁ አሉ።

ለአንድ ዓመት ከስራው ተባርሮ ሲያውደለድል የነበረው የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን ህላዊ ዮሴፍ ከነበረበት የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ተጠሪነቱ ተባርሮ የነበረ ሲሆን ታምራት ላይኔ ከእስር ቤት የተፈታ ሰሞን ወደ ስራ እንዲመለስ መደረጉ ታውቆዋል። ህላዊ ዮሴፍን ስራ ጀምሮዋል ለማሰኘት ብቻ የፈረሰው የማስታወቂያ ሚኒስትር የአሁኑ የቲሌቪዥን ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ ተደርጎ የተመደበ መሆኑን የገለፀው ዘገባ የበላዩ አለቃ ተደርጎ የተሾመው የህወሀቱ ታጋይ ዘርዓይ አስገዶም መሆኑን ጨምሮ አስረድቶዋል።

ቲሌቪዥንና ሬዲዮ አንድ ላይ የኮሚኒኬሽን መስሪያ ቤት ተብሎ በመለስ ስር እንዲሆን ተደርጎዋል። ይህ አዲስ የተዋቀረው የኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት በስሩ ቲሌቪዥን እና ሬዲዮ ድርጅቶችን ያካተተ ሲሆን ተጠሪነቱ ለመለስ ዜናዊ ሆኖ ከሱ ስር በረከት ስምኦን እንዲሆን የተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የቅንጅት አመራሮች በተከሰሱበት ወቅት አቃቤ ህግ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው ሆድ አደሩ ሽመልስ ከማል ደግሞ ዳይሬክተር ተብሎ የተሾመ መሆኑን ዘገባው አብራርቶዋል።